የትምህርት ማዕቀፉ ማስረጃዎች በተማሪዎች የትምህርት አፈፃፀም ላይ የተገኙ ውጤቶችን እና መሻሻል የሚያስገልጋቸውን ዘርፎች ያመለክታል።

ማርች 28፣ 2023 የትምህርት ቦርድ ስብሰባ ላይ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መሪዎች የተማሪዎችን እና የትምህርት ቤቶችን ስኬት ለመወሰን በርካታ ስልቶችን በመጠቀም በክፍል ደረጃ ብቃትን ማዳበር ላይ ያተኮረ የትምህርት ማስረጃ (EOL) የአመቱ አጋማሽ የዲስትሪክቱ አጠቃላይ መረጃ ቀርቧል። የ EOL ማዕቀፍ የተማሪዎችን የትምህርት አፈጻጸም ለመወሰን በርካታ መለኪያዎችን ይጠቀማል፤ ይህም የክፍል ውጤቶችን፣ ከስርአተ ትምህርት ጋር የተጣጣሙ ምዘናዎችን እና የስቴት እና ብሔራዊ ግምገማዎችን ያካትታል።

EOL የአጋማሽ አመት መረጃ MCPS ተማሪዎች እንዴት በተሳካ ሁኔታ ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላው እንደሚሸጋገሩ እንዲመረምር ያስችለዋል። መረጃው በመዋዕለ ህጻናት፣ 3ኛ፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት፣ 2ኛ፣ 5ኛ እና 8ኛ ክፍል እንዴት እንደተሸጋገሩ ማረጋገጫ ነጥብ ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ምን ያህል መመዘኛዎችን እያሟሉ እንደሆነ እና ለቀጣይ ስኬት የሚያስፈልጋቸውን ተጨማሪ ድጋፎች ለመወሰን እድል ይሰጣሉ።

EOL የሂሳብ ውጤቶች

በዚህ አመት ከመዋዕለ ህጻናት (K)፣ 3ኛ፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍል ቢያንስ ግማሽ ያህሉ ተማሪዎች ሂሳብ የተማሩበትን ማስረጃ አግኝተዋል፣ በዚህ አመት የመዋዕለ ሕፃናት ከፍተኛው መቶኛ (70.8%) የትምህርት ብቃት እና የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ብቃት ዝቅተኛውን መቶኛ (48.9%) ውጤት አሳይተዋል።

- **ከ 2021-2022 የትምህርት ማስተማመኛ ማስረጃዎች አመታዊ ሪፖርት ጋር ሲነጻጸር የዘንድሮው 3ኛ ክፍል ተማሪዎች 3 በመቶ-ነጥብ ጭማሪ አሳይተዋል፣ 6ኛ ክፍል ተማሪዎች 15 በመቶ-ነጥብ ጨምረዋል፣ እና 9ኛ ክፍል ተማሪዎች 2 በመቶ-ነጥብ ዝቅተኛ አሳይተዋል።**
- **ተማሪዎች ከበፊቱ የክፍል ደረጃቸው እንዴት እንደተሸጋገሩ በመመልከት፣ ጥቂቶች በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚጠበቅባቸውን እያሳኩ መሆናቸውን ሰራተኞቹ ያስተውላሉ።**
- **በዚህ አመት ከ 8ኛ ክፍል በ 2021-2022 ወደ 9ኛ ክፍል ሽግግር ሲደረግ በሂሳብ ትምህርት የታየው እድገት በ17.4 በመቶ ነጥብ ተሻሽሏል።**
- **በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኘው የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች/Emergent Multilingual Learners (EML) በ 3ኛ ክፍል 4 በመቶ ነጥብ፣ በ 6ኛ ክፍል 8 በመቶ ነጥብ እና በ 9ኛ ክፍል 5 በመቶ ነጥቦች መጨመሩ ታይቷል።**

በሂሳብ (2022 (SY) በሽግግር የትምህርት ዓመት እና SY (2023) የሚጠበቅባቸውን የሒሳብ ትምህርት ማስረጃ የሚያሟሉ ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት መቶኛ



የአገልግሎት ቡድኖች በመቶኛ ንጽፅር፡ ሽግግር SY 2022 vs SY 2023 በሂሳብ



የ 3ኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት ያገኙበት ማረጋገጫ መቶኛ ሲነጻጸር



የ 6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት ያገኙበት ማረጋገጫ መቶኛ ሲነጻፀር



የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት የሚጠበቅባቸውን ያሟሉ ንፅፅር በመቶኛ ማስረጃ



EOL የሊተርሲ ውጤቶች

በዚህ አመት ከመዋእለ ህጻናት (K)፣ 3ኛ፣ 6ኛ እና 9ኛ ክፍል ቢያንስ ግማሽ ያህሉ ተማሪዎች ሊተርሲ የሚጠበቅባቸውን የተማሩ መሆናቸውን ማረጋገጫ ያሳዩ ሲሆን ከፍተኛው በመቶኛ 9ኛ ክፍል (75.5%) እና ዝቅተኛው በመቶኛ 3ኛ ክፍል (52.6%) ነው።

ከ 2021-2022 አጋማሽ አመት የመማር ውጤት ማስረጃ ጋር ሲነጻፀር 3ኛ ክፍል የ 2 በመቶ-ነጥብ ቅናሽ፣ 6ኛ ክፍል የ10 በመቶ-ነጥብ ጭማሪ እና 9ኛ ክፍል 1 በመቶ-ነጥብ ጭማሪ የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ውጤት ንፅፅር ያሳያል።

የሚጠበቅባቸውን ትምህርት በማሳካት ረገድ በሊተርሲ የተማሪዎች አጠቃላይ የመማር ብቃት ማረጋገጫ በመቶኛ ንፅፅር (የሽግግር የትምህርት ዓመት (SY) 2022 ከ SY 2023)



የአገልግሎት ቡድኖች ንፅፅር መቶኛ፡ ሽግግር SY 2022 vs SY 2023 በሊተርሲ



3ኛ ክፍል ተማሪዎች በሊተርሲ የሚጠበቅባቸውን ትምህርት የመቅሰም ብቃት ማረጋገጫ በመቶኛ



6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሊተርሲ የሚጠበቅባቸውን ትምህርት የመቅሰም ብቃት ማረጋገጫ በመቶኛ



9ኛ ክፍል ተማሪዎች በሊተርሲ የሚጠበቅባቸውን ትምህርት የመቅሰም ብቃት ማረጋገጫ በመቶኛ



ቀጣይ እርምጃዎች

የክፍል ደረጃ የሚመጥን የትምህርት አሰጣጥን በሁሉም ትምህርት ቤቶች መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ ዲስትሪክቱ ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ በማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን የት/ቤት መሪዎችን የክፍል መምህራንን እንዲያሠለጥኑ እና እንዲደግፉ እያደረገ ነው። ይህ አካሄድ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ጣልቃገብነት እንዴት መታቀድ እንዳለበት ከትምህርት ቤቶች ጋር አብሮ መስራትን፣ እያደገ የመጣውን የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን እና እንዴት የማጠናከሪያ ትምህርት ወይም የማበልፀጊያ ትምህርት እድሎችን ስለመስጠት የማሻሻያ እርምጃዎችን ማቀድን ያካትታል።

በጊዜያዊነት በፀደቀው የ 2024 በጀት ዓመት የትምህርት ቦርድ በዲስትሪክቱ ውስጥ በሂሳብ እና በሊተርሲ ትምህርቶች ላይ ያተኮሩ ኢንቨስትመንቶች ላይ ያተኩራል። ይህም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሂሳብ እና የሊተርሲ ትምህርት ድጋፍን ለመጨመር ሱፐርቫይዘሮችን፣ የማስተማር ሰራተኞችን እና አሰልጣኞችን መጨመር፣ የት/ቤቶች ክትትል እና እድገት እንዲሁም ለሰራተኞች የሙያዊ እድገት እድሎችን ይጨምራል።

የሚቀጥለው EOL ቤንችማርክ - ወቅታዊ መረጃን ከትምህርት አመቱ መጨረሻ የትምህርት ውጤት ጋር በማነጻፀር – ፎል ላይ ለትምህርት ቦርድ ይቀርባል።

###